ጋዜጣዊ መግለጫ

# PRESS RELEASE

No.001/03 10 August 2010

Embargoed until Monday 16 August 2010

## ለፍሪጅ ጥገና ባለሙያዎችና ለቴክኒክና ሙያ ት/ቤቶች መምህራን መልካም የፍሪጅ ጥገና ዘዴ ላይ ያተኮረ ስልጠና በአራት ከተሞች  ይሰጣል፡፡

በኮምቦልቻ፣ ጎንደር፣ ጂማና ባሌ ሮቤ ከተሞች “Good Practices in Refrigerator Maintenance and Recovery and Recycling” በሚል ርዕስ ለፍሪጅ ጥገና ባለሙያዎችና የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ቤቶች ኦዞን የሚያሳሱ ኬሚካሎች ወደ ከባቢ አየር እንዳይገቡ ጥንቃቄ ማድረግ የሚያስችል በእያንዳንዱ ከተሞች ከነሐሴ 10 ጀምሮ የአምስት ቀናት ስልጠና ይሰጣል።

የስልጠናው ዓላማ ሀገሪቱ የገባችውን የሞንትሪያል ፕሮቶኮል በማስፈጸም ሂደት ውስጥ የፍሪጅ ጥገና ባለሙያዎች የመልካም የፍሪጅ አጠጋገን ዘዴዎችን በማሳወቅና ግንዛቤ በመፍጠርና ወደ ከባቢ አየር የሚለቀቀውን ኦዞንን የሚያሳሱ ኬሚካሎች መጠን መቀነስ ነው።

የሰልጣኞች ብዛት ስልጠናው በሚካሔድባቸው ከእያንዳንዱ ከተሞች አስራ ስድስት የፍሪጅ ጥገና ባለሙያዎች (ቴክኒሻኖች)ና ዘጠኝ የቴክኒክና ሙያ ትቤቶች መምህራን በስልጠናው ይሳተፋሉ ፡፡

በመጀመሪያዎቹ ሶስት ቀን ተኩል ስለ ኦዞን ሽፋንና ጠቀሜታው፣ የኦዞንን ሽፋን የሚያሳሱ ኬሚካሎች አይነትን አማራጭ ኬሚካሎች፣ የፍሪጅና የኤር ኮንዲሽነር ሲስተምና በጥገና ወቅት ሊደረጉ የሚገባቸው ጥንቃቄዎች እንዲሁም የማቀዝቀዣ ፈሳሾችን በጥገና ወቅት ሪከቨር ማድረግና ጥገናው ከተጠናቀቀ በኋላ እንደገና መጠቀም የሚያስችል የቲዎሪ ትምህርት ይሰጣል። በቀሪው አንድ ቀን ከግማሽ ደግሞ በሪከቨሪና ሪሳይክሊንግ ዙሪያ የተግባር ስልጠና ይሰጣል፡፡ ስልጠናው በቅድሚያ ኮምቦልቻና ደሴ በመቀጠል ደግሞ ጂማና ባሌ ሮቤ ከተሞች ላይ ይሰጣል፡፡

ስልጠናው ከዚህ ቀደም በመስኩ ጀርመን ሐገር ሰልጥነው በመጡ ከፍተኛ ባለሙያ እንደሚሰጥና የስልጠናው ወጪ በመልቲላተራል ፈንድ የገንዘብ ድጋፍ መከናወኑ ታውቋል።

በብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ የሕግ፣ ዓለም ዓቀፍና ሕዝብ ግንኙነት Aገልግሎት ስልክ 0115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡
nmsa@ethionet.et / forhailuwpro@yahoo.com